በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ባለሥልጣን
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE REVENUE AUTHORITY
☎ 058-220-4694 or 058-220-9305
058-220-9307 or 058-220-9308
✉ 746
Fax 058-220-9297

30(8)

ቁጥር ________
ቀን ________

ለ ____ ዞን ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት
________ ፡
ለ ____ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት
________ ፡

ጉዳዩ፡- **የፀደቁ አዋጆችን ስለማሳወቅ፣**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 161/2001 ዓ.ም መፅደቁን በቁጥር አብክ12/725/መ/ክ-3 በቀን 03/04/2001 ጠቅሶ የላከልንን 9 ገፅ ፎቶ ኮፒ መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ//

- ለምክትል ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለገቢ አሰባሰብና ክትትል ዋና የስራ ሂደት

ገቢዎች ባለስልጣን

ባህር ዳር፣

ባህር ዳር ----- ቀን 2001 ዓ.ም

አዋጅ ቁጥር 161/2001ዓ.ም.

# በአማራ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መወሰኛ አዋጅ

## አዋጅ ቁጥር 161/2001ዓ.ም

## በአማራ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መንግሥት ለአርሶ አደሩ ምርት ዕድገት አስተዋጽኦ ያላቸውን የግብርና ግብአቶች በአይነት፣ በመጠንና በወቅቱ እንዲቀርቡለትና ገበያ መር የግብርና አመራረት ዘዴን እንዲከተል በማድረግ በትንሽ መሬት ብዙ ምርት ማምረት የሚችልበትን ሁኔታ እና ላመረተው ምርት ምቹ የገበያ ሥርዓት በመፍጠር የምርቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረጉ የአርሶ አደሩ ገቢ ያደገ በመሆኑ፤

በሁሉም የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ ንፁህ መጠጥ ውኃ እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሟሉለትና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲፈቱለት አርሶ አደሩ የሚያቀርበው ጥያቄ እያደገ በመምጣቱ የተነሣ ተጨማሪ የፋይናንስ አቅም የሚያስፈልግ ሆኖ በመገኘቱ፤

በስራ ላይ ያለው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 30/1991 ዓ.ም አሁን ካለው ተጨባጭ አገራዊና ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ፤

የክልሉን ልማት ይበልጥ ለማረጋገጥ እየተደረገ ያለውን ጥረት ቀጣይነት ባለው መንገድ በበለጠ አጠናክሮ ለማስኬድ የፖሊሲ ድጋፍ የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 161/2001 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የገጠር መሬት" ማለት አርሶ አደሩ ለእርሻ ሥራ አገልግሎት የሚጠቀምበት ወይም በየትኛውም አካባቢ በአርሶ አደር ይዞታ ሥር ያለ መሬት ማለት ነው፡፡
2. "አርሶ አደር" ማለት በዋነኛነት የራሱን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት እና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት የእርሻ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም በግል የሚሰራ ሰው ወይም የአርሶ አደር ኅብረት ስራ ማኅበር አባል ሆኖ በወል የሚሰራ ነው፡፡
3. "ክፍያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ነው፡፡

4. "የገቢ ግብር" ማለት የመሬት ይዞታ መጠንን መሠረት በማድረግ ከእርሻ ሥራ ገቢ በሚገኝ ጥቅም ላይ ታስቦ የሚከፈል ግብር ነው፡፡

5. "የመሬት ይዞታ" ማለት በአንድ አካባቢ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ በአርሶ አደር ስም የተመዘገበና ለእርሻ ሥራ የተያዘ መሬት ሲሆን ወጀድን /ጓሮን/ ይጨምራል፡፡

6. "በምግብ ዋስትና የታቀፉ ቀበሌዎች" ማለት የክልሉ መንግሥት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር በታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች የሚገኙበት ነው፡፡

7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

8. "ግብር ሰብሳቢ" ማለት የቀበሌ አስተዳደር ወይም የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እንዲሰበሰብ በሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር የሚወከል ሰው ነው፡፡

9. "ግብር አስገቢ መ/ቤት" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለስልጣ ነው፡፡

10. "ባለስልጣን" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለስልጣ ነው፡፡

11. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ነው፡፡

12. "መንግሥት" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ

3. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያን ስለመክፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ለያዘው የገጠር መሬት አገልግሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተወሰነውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

4. ስለ ገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚገኝ ማንኛውም አርሶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን እንደሚከተለው ተወስኗል፡፡

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን /በሄክታር/ | የመሬት መጠቀሚያ የክፍያ /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 0.5 ሄ/ር | 15 |
| 2 | ከ0.5 በላይ እስከ 1.0 ሄ/ር | 20 |
| 3 | ከ1.0 በላይ እስከ 1.5 ሄ/ር | 25 |
| 4 | ከ1.5 በላይ እስከ 2.0 ሄ/ር | 30 |
| 5 | ከ2.0 በላይ እስከ 2.5 ሄ/ር | 35 |
| 6 | ከ2.5 በላይ እስከ 3.0 ሄ/ር | 40 |

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር በታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖር አርሶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን/በሄክታር/ | የመሬት መጠቀሚያ የክፍያ /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 0.5 ሄ/ር | 10 |
| 2 | ከ0.5 በላይ እስከ 1.0 ሄ/ር | 15 |
| 3 | ከ1.0 በላይ እስከ 1.5 ሄ/ር | 20 |
| 4 | ከ1.5 በላይ እስከ 2.0 ሄ/ር | 25 |
| 5 | ከ2.0 በላይ እስከ 2.5 ሄ/ር | 30 |
| 6 | ከ2.5 በላይ እስከ 3.0 ሄ/ር | 35 |

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተጠቀሰው ይዞታ መጠን ውጪ ከ3 ሄክታር በላይ የመሬት ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች በየግማሽ /0.5/ ሄክታር ተጨማሪ ይዞታ ብር 15/አስራ አምስት ብር/ ይከፍላሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ እርሻ ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል

5. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ስለመክፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ከተሰማራበት የእርሻ ሥራ በሚያገኘው ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ የተወሰነውን ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

6. ስለ እርሻ ሥራ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን

1. በአማራ ብሄራዊ ክልል የሚገኝ ማንኛውም አርሶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ተመን እንደሚከተለው ተወስኗል፡፡

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን /በሄክታር/ | የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 0.5 ሄ/ር | 25 |
| 2 | ከ0.5 በላይ እስከ 1.0 ሄ/ር | 35 |
| 3 | ከ1.0 በላይ እስከ 1.5 ሄ/ር | 50 |
| 4 | ከ1.5 በላይ እስከ 2.0 ሄ/ር | 70 |
| 5 | ከ2.0 በላይ እስከ 2.5 ሄ/ር | 95 |
| 6 | ከ2.5 በላይ እስከ 3.0 ሄ/ር | 130 |

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር በታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖር አርሶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የመሬት ይዞታ መጠን/በሄክታር/ | የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 0.5ሄ/ር | 20 |
| 2 | ከ0.5 በላይ እስከ 1.0ሄ/ር | 30 |
| 3 | ከ1.0 በላይ እስከ 1.5ሄ/ር | 40 |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ከ1.5 በላይ እስከ 2.0ሄ/ር | 55 |
| 5 | ከ2.0 በላይ እስከ 2.5ሄ/ር | 75 |
| 6 | ከ2.5 በላይ እስከ 3 ሄ/ር | 105 |

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ከ3 ሄክታር በላይ የመሬት ይዞታ መጠን ያላቸው አርሶ አደሮች በእያንዳንዱ ተጨማሪ ግማሽ ሄክታር /0.5 ሄክታር/ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ብር 25/ሃያ አምስት ብር/ ይከፍላሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ ግብር አሰባሰብና ስለ ግብር አስገቢ አካላት ስልጣንና ተግባር

7. ስለ ክፍያና ግብር ተመን ስሌት

የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መጠን ተሰልቶ የሚወሰነው እያንዳንዱ አርሶ አደር ባለው የመሬት ይዞታ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡ አከፋፈሉም ሁለቱንም በአንድ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ተዳምሮ የሚከፈል ወይም የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

8. ስለ ግዴታዎች

ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 እና 6 የተወሰነውን ግብር በአዋጁ አንቀጽ 9 ስር በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢ አካላት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

9. ስለ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የሚሰበሰበው በበጀት ዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም በፈቃደኝነት ማንኛውም አርሶ አደር ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ የተጣለበትን ክፍያና ግብር መክፈል ይችላል፡፡

10. ስለ ግብር ሰብሳቢው ግዴታ

ማንኛውም ግብር ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የሰበሰበውን የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለሚመለከተው ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

11. ስለ ግብር ሰብሳቢው አካል

በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው እያንዳንዱ የቀበሌ መስተዳድር ከቀበሌው አመራር ውስጥ መርጦ በሚወክለው ሰው የሚሰበሰብ ሲሆን የተመረጡ ሰዎችን ዝርዝር የቀበሌው መስተዳድር አስቀድሞ ለገቢዎች ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡

12. የአርሶ አደር ዝርዝር ስለማሳወቅ

ማንኛውም የቀበሌ አስተዳደር በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ስም ዝርዝር ከመሬት ይዞታ መጠናቸው ጋር በየበጀት ዓመቱ ከመስከረም 30 ቀን በፊት ለወረዳው መስተዳድር የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

13. ስለ ወረዳው መስተዳደር ኃላፊነት

እያንዳንዱ የወረዳ መስተዳድር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 የተላከለትን ዝርዝር እንደደረሰው ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

14. ስለ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ግዴታ

የወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት የተላለፈለትን ዝርዝር ከሰበሰበዉ ዓመታዊ ገቢ ጋር አመሳክሮ ውጤቱን ለወረዳው መስተዳድር የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

15. ስለ ውሳኔ አፈፃፀም

ማንኛውም አርሶ አደር የተወሰነበትን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር በአዋጁ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆን

የመክፈያው ጊዜ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በማናቸውም ጊዜ የቀበሌ አስተዳደሩ በሚመለከተው የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ክስ መስርቶ የማስፈፀሚያ ትዕዛዝ ሊያሰጥበት ይችላል ወይም የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ ክስ ሊመሠረት ይችላል፡፡

16. ደረሰኝ ስለመስጠት

1. ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈጽመው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ከግብር ሰብሳቢው ሕጋዊ ደረሰኝ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. ስለመቀጫ

ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሳይከፍል ከቀረ ክፍያው ወይም ግብሩ በዘገየበት በእያንዳንዱ ወር ብር አምስት /5/ ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው መጠን ከግብሩ መብለጥ የለበትም፡፡

18. ስለ አበል

የቀበሌ መስተዳድር በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ሁለት በመቶ / 2%/ በኮሚሽን መልክ ይሰጠዋል፡፡ ክፍፍሉን በተመለከተ ደንብና መመሪያ ሊወጣ ይችላል፡፡

19. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡